# የንጥር-ጥናት አውትላይኖች
# አንደኛ እና ሁለተኛ ሳሙኤል

## ቁልፍ መግለጫዎች

የእግዚአብሔር መንግሥት ይመጣ ዘንድ
በ 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል ሦስታንዱ አምላክ
ከአካል መልበሱ እና ከቤዛነቱ ጋር
ሳሙኤልን እና ዳዊትን በማምጣት ውስጥ ሙሉ በሙሉ እንደተሳፈ ማየት እንችላለን፤
ሦስታንዱ አምላክ ዛሬ ፈቃዱን ለማከናወን፣ ዓላማውን ለመፈጸም
እና የልቡን መሻት ለማርካት በእኛ ውስጥ እየሠራ
ከእኛ ጋር መሆኑን ማየታችን በጣም አስፈላጊ ነው።

ከመጸለይ ውጪ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ከፍተኛ ጫፍ፣
የክርስቶስ አካል እውነታ ጋር የሚደረስበት ሌላ መንገድ የለም፤
የክርስቶስ ሙሽራ ለመሆን እንደ የክርስቶስ አካል እውነታ ድል ነሺዎች መሆናችን
ይህን ዘመን፣ የቤተ ክርስቲያንን ዘመን ይዘጋዋል፣
እንዲሁም በመንግሥቱ ዘመን ከድል ነሺዎቹ ጋር
ይህችን ምድር ለመውሰድ፣ የራሱ ለማድረግ እና ለመግዛት
ክርስቶስን እንደ የክብር ንጉሥ መልሶ ያመጣዋል።

የእግዚአብሔር ልጅ የነበረው ክርስቶስ
በተሠግዎው፣ በመሰቀሉ እና በትንሣኤው፣
በስብዕና የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ በመሰየም
በአዲስ መንገድ የእግዚአብሔር ልጅ—በኩሩ ልጅ—ሆነ፤
በሮሜ 1፡3-4 የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ማራቢያው ሞዴል ሲሆን፣
በሮሜ 8፡29 ያሉት ብዙ ወንድሞች ደግሞ ከማራቢያ ሞዴሉ "በአንድ ጊዜ-የፈሩ"
እና በሕይወት በመዳን የበኩሩን ልጅ
መልክ የሚመስሉት ናቸው።

የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ራሱን ወደ ውስጣችን መሥራት ነው፣
ይህም በተፈጥሮአዊ ሕይወታችን ቀስ በቀስ የሆነ
እና ውስጠ-መሠረታዊ የገንባ-አፍራሽ ቅንባሮ ለውጥ የሆነውን መለወጥን የሚያመጣውን
የመንፈሳዊ መብላላትን እና መዋሐድን
ገንባ-አፍራሽ ቅንባሮ ሂደት እንለማመድ ዘንድ ነው፤
ይህ አዲስቱ ኢየሩሳሌምን ለማጠናቀቅ ለክርስቶስ አካል መገንባት ነው።

*© 2021 Living Stream Ministry*

መልእክት አንድ

## የ 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል ማዕከላዊ ኃሳብ እና
## መለኮታዊው ሥላሴ በ 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል እንደተገለጠው

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ 1 ሳሙ. 1፡3፣ 7፣ 10-11፣ 19-24፤ 2፡11፣ 35፤
3፡9-11፣ 21፤ 7፡3-6፤ 8፡4-22፤ 16፡1-3፣ 13፤ 2 ሳሙ. 23፡1-3፤ 24፡25

**I. የ 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል ማዕከላዊ ኃሳብ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ እንዲፈጸም የሰው ትብብር ያስፈልገዋል—የተሠግዎ መርህ፦**

ሀ. የተሠግዎ መርህ እግዚአብሔር ሰውን ከራሱ ጋር አንድ ለማድረግ ወደ ሰው ውስጥ መግባቱ እና ራሱን ከሰው ጋር ማዋሐዱ ነው፤ ስለዚህ፣ እግዚአብሔር በሰው ውስጥ ነው ሰውም በእግዚአብሔር ውስጥ ነው፣ አንድ ሕይወት እና አንድ ኑሮም አላቸው—ዮሐ. 15፡4-5፤ ገላ. 2፡20።

ለ. የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መፈጸም ትብብራችንን በመጠየቁ ሃቅ በጣም ልንደነቅ ያስፈልገናል፤ ከእግዚአብሔር ጋር መተባበር ማለት ከእግዚአብሔር ጋር በአንድ ላይ መታሰር ማለት ነው—1 ቆሮ. 6፡17፤ ዮሐ. 15፡4-5፤ 2 ቆሮ. 6፡1፤ 1 ቆሮ. 3፡9፤ 16፡10፣ 16።

ሐ. በ 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል ከእግዚአብሔር ጋር መተባበር በሳሙኤል እናት በሐና፣ በሳሙኤል እና በዳዊት አዎንታዊ በሆነ መልኩ እና በኤሊ እና በሳኦል አሉታዊ በሆነ መልኩ በምሳሌ ተገልጿል።

መ. በተሠግዎ መርህ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር መተባበር ሁሉን-ያካተተውን እና ሁሉን-ደረስ የሆነውን ክርስቶስ በምሳሌ ከምታሳየው ከመልካሚቱ ምድር የግል ድሰታ ጋር ይገናኛል—ዘዳ. 8፡7-10፦

1. አንደኛ እና 2ኛ ሳሙኤል፣ እንደ ኢያሱ፣ መሣፍንት እና ሩት መቀጠል፣ በእግዚአብሔር-የተሰጠውን የመልካሚቱን ምድር ድሰታ በተመለከተ ዝርዝር ይሰጣሉ።
2. በ 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል ያሉት ምሳሌዎች ለእግዚአብሔር መንግሥት፣ ለቤተ ክርስቲያን መመሥረት የአዲስ ኪዳን አማኞች ክርስቶስን በእግዚአብሔር እንደተሰጣቸው እድል ፈንታ እንዴት መደሰት እንደሚችሉ እና እንዴት መደሰት እንዳለባቸው ያሳዩናል—ቆላ. 1፡12፤ ማቴ. 16፡18-19፤ ሮሜ 14፡17፦
   ሀ. በ 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል ከእግዚአብሔር ጋር የተባበሩ ሰዎች የተደሰቷት መልካሚቱ ምድር የእግዚአብሔር መንግሥት ሆነች።
   ለ. ከእግዚአብሔር ጋር በምናደርገው ትብብር የክርስቶስ ድሰታችን ከክርስቶስ ጋር በሕይወት የምንገዛበት የእግዚአብሔር መንግሥት እስከሚሆንበት መጠን ድረስ ክርስቶስን መደሰት ያስፈልገናል—ሮሜ 5፡17፤ 14፡17።

**II. በ 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል እንደተገለጠው መለኮታዊውን ሥላሴ ማየት ያስፈልገናል፦**

ሀ. ለተመረጡት ሕዝቡ ያለው የእግዚአብሔር ዓላማ ጠላቶችን ማሸነፍ እና መልካሚቱን ምድር በሙላት የራስ ማድረግ ብቻ ሳይሆን በምድሪቱ ላይ መንግሥትን መመሥረት ነበር፦

1. እግዚአብሔር መገለጡን የማግኘትን ውጥኑን ለመፈጸም፣ መንግሥት፣ የሚገለጥበት ክልል ሊኖረው ያስፈልጋል—1 ሳሙ. 10፡25፤ ማቴ. 6፡10፤ ሉቃ. 1፡33።
2. የእስራኤል ልጆች ከግብጽ የእግዚአብሔርን ማደሪያ ድንኳን ወደገነቡበት ወደ ምድረበዳ ወጡ፤ ከዚያም ወደ መልካሚቱ ምድር ገቡ፣ እግዚአብሔር በምድር ላይ መንግሥት ይኖረው ዘንድ እያንዳንዱ ነገድ ከምድሪቱ የተወሰነ ድርሻ ተሰጠው—ኢያ. 13፡1—22፡34።
3. አንደኛ እና 2ኛ ሳሙኤል ለመንግሥቱ መምጣት ወሳኝ ናቸው—1 ሳሙ. 8፡4-22፤ 10፡25፤ 13፡14፤ 15፡28፤ 16፡1-3፣ 13።

ለ. በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ ካለው አሳዛኝ ሁኔታ የተነሣ፣ እንደ ሳሙኤል ያለ ሰው የማግኘት አስቸኳይ እና ከፍተኛ ፍላጎት ነበረ—1 ሳሙ. 2፡35፤ 3፡21፦

1. ሳሙኤል ናዝራዊ፣ ካህን፣ ነቢይ እና መስፍን ነበር፤ ንጉሡን ማምጣት እና መንግሥቱን መመሥረት የሚችል እንዲሆን ይህ አራት እጥፍ ደረጃ ብቁ አደረገው።
2. ሳሙኤል ካህን፣ ነቢይ እና መስፍን መሆኑ የእግዚአብሔር ግብ አልነበረም፤ የእግዚአብሔር ውጥን ንጉሥ ያለው መንግሥትን መመሥረት ነበር—8፡7፤ 13፡14።

ሐ. አንደኛ እና 2ኛ ሳሙኤል ንጉሡን ማምጣት እና መንግሥቱን መመሥረት መለኮታዊው ሥላሴ ከሕዝቡ ጋር በመሆኑ ላይ እንደተመረኮዘ ይገልጣሉ፦

1. እንደ ሳሙኤል ያለ ሰው ለመነሣቱ እና ተልዕኮውን ለመፈጸሙ፣ የመለኮታዊው ሥላሴ አስፈላጊነት ነበር—1 ሳሙ. 1፡10-11፣ 20፤ 10፡1፣ 6፤ 16፡1-3።
2. በዚህም ምክንያት፣ በ 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል የመለኮታዊው ሥላሴ ዝርዝር፣ የላቀ መገለጥ አለ፤ በ 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል በተዘገበው ታሪክ ውስጥ ወሳኙ ነጥብ የመለኮታዊው ሥላሴ አስፈላጊነት መኖሩ ነበር—2 ሳሙ. 22፡1-3፤ 23፡1-3፤ 24፡25።

መ. መለኮታዊው ሥላሴ እና የጌታ ሉአላዊ እጅ በ 1ኛ ሳሙኤል 1 ተገልጠዋል፡-

1. በዘቀጠችው እስራኤል ቀውስ መካከል፣ ሕልቃና እና ሐና ለዘላለማዊ አላማው በእግዚአብሔር በተወሰነው የሕይወት መንገድ ላይ ቆዩ—ቁ. 1-5፣ 10-11፣ 20፣ 24።
2. ሕልቃና ያህዌን ለማምለክ እና መሥዋዕቶችን ለማቅረብ በየዓመቱ ከቤተሰቡ ጋር በዚያን ጊዜ በሴሎ ወደ ነበረው ወደ እግዚአብሔር ቤት፣ ወደ ማደሪያው ድንኳን ይወጣ ነበር—ቁ. 3፣ 21-24፡-
   ሀ. በ ቁጥር 3-7፣ 10-11፣ 20 እና 24 መሥዋዕቶቹ ክርስቶስን እና መሥዋዕቶቹን ሁሉ በምሳሌ ያሳያሉ፤ ወይፈኖቹ፣ ዱቄቱና የወይን ጠጁ የምንለማመደውን እና ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ወደ እግዚአብሔር ቤት የምናመጣውን ክርስቶስን ያመለክታሉ።
   ለ. ያህዌ ታላቁ እኔ ነኝ ነው፣ የያህዌ ቤት በሕዝቡ መካከል የእግዚአብሔር ማደሪያ ስፍራ ለመሆን የእግዚአብሔር አካል መልበስ የሆነው ክርስቶስ ነው—ቁ. 10-11።
   ሐ. ይህ ክፍል በዋናነት የሚያሳየው የሦስታንዱ አምላክ አካል መልበስ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቤት እና ወደ እግዚአብሔር አካል መልበስ ውስጥ የምንገባበት መንገድ፣ ማለትም፣ ቤዛነት የሆኑትን መሥዋዕቶቹን ነው፤ ስለዚህ፣ በእነዚህ ጥቅሶች የእግዚአብሔርን አካል መልበስ እና የእግዚአብሔርን ሙሉ ቤዛነት እናያለን—ተዛ. የሐ. 1፡14፣ 29፤ ሉቃ. 1፡68፤ 2፡38፤ ኤፌ. 1፡7።
3. ያህዌ የሐናን ማኅፀን ስለዘጋ፣ የተሰጠ እና የሚሰጥ ጸሎት ለመጸለይ ተገደደች፤ ሉአላዊ እና ምሥጢራዊ በሆነ መልኩ በእግዚአብሔር በመነሣሣት፣ ለጌታ ፍጹም የሚሆን ወንድ ልጅን ለማግኘት ጸለየች—1 ሳሙ. 1፡5፣ 10-12፣ 15።

ሠ. በ 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል የእግዚአብሔር መንግሥት ይመጣ ዘንድ ሦስታንዱ አምላክ ከአካል መልበሱ እና ከቤዛነቱ ጋር ሳሙኤልን እና ዳዊትን በማምጣት ውስጥ ሙሉ በሙሉ እንደተሳተፉ ማየት እንችላለን፡-

1. መለኮታዊው ሥላሴ ዳዊት ንጉሥ ለመሆን በመቀባቱ ውስጥ ተገልጧል—1 ሳሙ. 16፡1-3፣ 13፡-
   ሀ. በእነዚህ ጥቅሶች ሦስታንዱን አምላክ እንደ ያህዌ እንዲሁም የሦስታንዱን አምላክ መንፈስ እንደ ያህዌ መንፈስ እናያለን—ቁ. 13።
   ለ. ዘይቱ የእግዚአብሔርን መንፈስ በምሳሌ ያሳያል፣ የተሠዋችው ጊደር ክርስቶስን እንደ መሥዋዕቱ በምሳሌ ታሳያለች፤ ስለዚህ፣ መለኮታዊው ሥላሴ ዳዊትን እስራኤል ላይ ንጉሥ እንዲሆን በማድረግ በዳዊት መቀባት ውስጥ ተሳትፏል—መዝ. 89፡20።
2. በ 2ኛ ሳሙኤል 22፡1-3 ዳዊት ለያህዌ የዘመረው መዝሙር ቃሎች ያህዌን እንደ ቋጥኙ፣ አምባው፣ መድኃኒቱ፣ ዓለቱ፣ እና ጋሻውና የመዳን ቀንዱ ይጠቅሳሉ፤ በቁጥር 47 ዳዊት "እግዚአብሔር ሕያው ነው፥ ጠባቂዬም ቡሩክ ነው፤ የመድኃኒቴ ጠባቂ አምላኬ ከፍ ከፍ ይበል" በማለት ያውጃል።
3. በ 2ኛ ሳሙኤል 23፡1-3—በዳዊት የመጨረሻ ቃሎች—የያህዌ መንፈስ በእርሱ በኩል ተናገረ፣ የእስራኤልም ዓለት ተናገረው—ቁ. 2-3፡-
   ሀ. በእነዚህ ጥቅሶች ዓለቱ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ጸጋ የሚሰጥበት መቆሚያ የሆነው ክርስቶስ ነው።
   ለ. የያህዌ መንፈስ የሦስታንዱ አምላክ መንፈስ ነው—1 ሳሙ. 10፡6፤ 16፡13።
   ሐ. በእነዚህ ጥቅሶች *እግዚአብሔር* በዕብራይስጥ *ኤሎሂም* ነው፣ ይህም ሦስታንዱን አምላክ ያመለክታል።
4. በ 2ኛ ሳሙኤል 24፡25 የሚቃጠለው መሥዋዕቶች ለእግዚአብሔር እርካታ የሆነውን ክርስቶስን በምሳሌ ያሳያሉ፣ የሰላም መሥዋዕቶቹ ደግሞ በእግዚአብሔር እና በሕዝቡ መካከል ላለ ሰላም ክርስቶስን በምሳሌ ያሳያል።

**III. የአሁኑ ሁኔታችን እና የእግዚአብሔር ፍላጎት በሳሙኤል ጊዜ ከነበረው ሁኔታ እና ፍላጎት ጋር በመርህ አንድ አይነት ናቸው—1 ሳሙ. 8፡4-22፡-**

ሀ. አንዳንዶች ሐና እንዳደረገችው ለእግዚአብሔር ግብ ተጽዕኖ የሚያመጡ ጸሎቶችን እንዲጸልዩ እና ብቁ የሆኑት በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ያለውን ግራ የተጋባ ሁኔታ ለማቆም እና ንጉሡን እና መንግሥቱን ለማምጣት

እግዚአብሔር እንደተጠቀመበት እንደ ሳሙኤል—ናዝራዊ፣ ካህን፣ ነቢይ እና የመጨረሻው መስፍን—የመሆናቸው አስቸኳይ ፍላጎት አለ—2፡35፦

1. ዛሬ የእግዚአብሔርን ፍላጎት ለማሟላት እንጸልይ ዘንድ፣ ክርስቶስ እንደ ሦስታንዱ አምላክ አካል መልበስ እና እንደ መሥዋዕቶቹ ሁሉ እውነታ ያስፈልገናል፣ የመገናኛው ድንኳን እውነታ ማለትም የእግዚአብሔር ማደሪያ ስፍራ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ታስፈልገናለች—ቆላ. 2፡9-10፤ ኤፌ. 2፡21-22፤ ዕብ. 8፡1-2፤ 10፡8-10።
2. በአንድ በኩል ንጉሣችን ክርስቶስ ገና በዚህ የለም፣ እኛም እንደ መሣፍንት ዘመን ግራ በተጋባ ሁኔታ ውስጥ ነን—መሳ. 21፡25።
3. የእግዚአብሔር መንግሥት መፈጸም በጌታ ኢየሱስ የሚመጣው የመንግሥቱ መምጣት ነው፣ ነገር ግን እንደ ሳሙኤል ያሉ አንዳንዶች መንግሥቱን በማምጣት ከመለኮታዊው ሥላሴ ጋር ሊተባበሩ ያስፈልጋል—ማቴ. 6፡33፤ 1 ቆሮ. 6፡17፤ 16፡10፤ 2 ቆሮ. 6፡1።
4. ተጽዕኖ ያላቸውን ጸሎቶች ለመጸለይ እና መንግሥቱን ለማምጣት መለኮታዊው ሥላሴ ምን ያህል እንደሚያስፈልግ መገንዘብ ያስፈልገናል—ማቴ. 6፡10፣ 13፤ ራእ. 1፡4-7፤ 8፡3-5።

ለ. ሦስታንዱ አምላክ፣ ከአካል መልበሱ፣ ከቤዛነቱ እና ከመንፈሱ ጋር ለመምጣቱ እና ለመንግሥቱ ጠቃሚ ሰዎች አድርጎ እያቀናበረን ነው—2 ቆሮ. 13፡14።

ሐ. ሦስታንዱ አምላክ ዛሬ ፈቃዱን ለማከናወን፣ ዓላማውን ለመፈጸም እና የልቡን መሻት ለማርካት በእኛ ውስጥ እየሠራ ከእኛ ጋር መሆኑን ማየታችን በጣም አስፈላጊ ነው—ፊልጵ. 2፡13፤ ዕብ. 13፡21፤ ኤፌ. 1፡5፣ 9፣ 11፤ 5፡17፤ ቆላ. 1፡9፤ ሮሜ 12፡2፤ ራእ. 4፡11፦

1. ይህን ራእይ ካየን፣ ክርስቲያን መሆን ምን ማለት እንደሆነ ያለንን ጽንሰ-ኃሳባችንን ሥር-ነቀል በሆነ መልኩ ይለውጠዋል—ሐዋ. 26፡19፤ ሮሜ 12፡7-8፤ 2 ቆሮ. 5፡14-15፤ ኤፌ. 3፡16-17።
2. የክርስቲያን ሕይወትን በተመለከተ ያሉን ተፈጥሮአዊ፣ ኃይማኖታዊ፣ ባሕላዊ፣ ግብረገባዊ፣ እና ሥነ-ምግባራዊ ጽንሰ-ኃሳቦች ሙሉ በሙሉ ከእኛ ጋር በሆነው ሦስታንዱ አምላክ ራእይ መተካት ያስፈልጋቸዋል—ማቴ. 28፡19፤ 2 ቆሮ. 13፡14፤ ኤፌ. 4፡4-6፤ ራእ. 1፡4-7።

© 2021 Living Stream Ministry